# የብርሃኑ ነጋ ወይስ የኢትዮጵያውያን የስፖርት ፌዴሬሽን?

ኢድሪስ ብርሃኑ

የሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያውያን ስፖርት ፌዴሬሽን ለድያስፖራ ዜጎች መሰብሰቢያና በተለይም ለትግሬዎቹ ቡድን ውድቀት ፈላጊዎች መገናኛ ይሆናል በሚል ባለፉት ዓመታት በወያኔና አላሙዲ የደረሰበትን ጥቃት ተከላክለው ህልውናውን የጠበቁለት ኢትዮጵያውያን ብዙዎች ናቸው ። የፌደሬሽኑ ዋና ባለስልጣኖች ግን (በተለይ የግንቦት 7 አባል ወይም ደጋፊ የሚባለው ፕሬዚዳንት ጌታቸው ተሰፋዬና ምክትሉ) የወገንተኝነትን ካባ መልበስ መርጠው ሊደብቁ ቢሞክሩም የብርሃኑ ነጋ ሰራተኞች መሆናቸውን በቅርቡ በጁላይ 4 ባለቀውም በዓል አስመስክረዋል ።

ይህን ያልኩበት ምክንያት ብርሃኑ ነጋ እንደ አዛዥ ናዛዥ በቁምጣና ነጠላ ጫማ ሲወዛወዝ በማየቴ ብቻ ሳይሆን ለግንቦት7/ /ኢሳት የተሰጠውን ልዩ ቦታም በግምት በማስገባት ነው ። በሜዳው ኢሳትና ህዝባዊ ሀይል በሚል በርካታ መደቦች/ድንኳኖች ነበሩ ። ኪነት ሲባልም ሰው የጠፋ ይመስል ታማኝ ከነሚስቱ ቦታን ይዟል ።ለቶምቦላ የቀረበችው መኪናን ቲኬት ሻጮች የብርሃኑ ተከታዮች ነበሩ ።ለመዝጊያው ቀን የዘፈን ምሽትም ወደ 50 ነጻ ቲኬት ለነብርሃኑ ብቻ በፌዴሬሽኑ ተለግሷል ። የተጭበረበሩ መግቢያ ቲኬቶችንም ሲሸጡ የታዩ ነበሩ ።ለዘፈኑ ምሽትም መደበኛው ቲኬት 50 ዶላር ሲሆን በጎን በሀያና አስር ዶlaርም ወደ ኢትዮጵያ መሬት ዘልቀን ሳይቀር የሚሸጡት እነማን ነበሩም፡ ለምንስ ፌደሬሽኑ አይቶ እንዳላየ ሆነ ሲባል መልሱ ይህን ያህል ከባድ የሚሆን አይደለም ። ግንቦት7 ከዚህ ዓመት የእግር ኳስ ውድድር በሰፊው አትርፏል። ፌዴራሽኑ ግን ስሙንና ነጻነቱን አጉዱፏል ።

የብርሃኑ ነጋ ግንቦት 7 መንምኖ እንደሚገኝ የአደባባይ ምስጢር ነው ። ቴሌቪዥኑ የተቋረጠው በወያኔ ጫና ሳይሆን በራሱ ውስጣዊ ቀውስ መሆኑ ሊደበቅ አልቻለም ። ብርሃኑ ሁሉም ገንዘብ ወደ ኪሴ ባይ ነውና ድርጅቱ የገንዘብ ዕጥረት አለበት ሲባልም ውሎ አድሯል ። በአሁን ጊዜ ጥራት በጎደለው በሩስያ ሳተላይት የጀመረው የቲቪ ስርጭትም ምን ያህል ይበረክታል የሚለው አጠያያቂ ነው ። መዋጮ ከፋይ ቁጥርም ቅርንሷል ። ድርጅቱ ራሱን ወደ ኤርትራ ሄዶና ነፍስ ገዳዩን ሻዕቢያን አሞግሶ ወደ ዝቅጠት ከከተተ ጀምሮ በርካታ አባላት ትተውታል ። ዌንዲ ሸርማንም ብትሆን የአሜሪካንን ፖሊሲ አቅጣጫ ጠቁማለች ። የቸገረው እንደተባለው ሆነና ጦር አልባው ግንቦት 7 በትግራይ መሬት ጥቃት አደረስኩ ሲል--የኮለኔል ጎሹ "ጦር" ይል እንደነበረው 50 ገድዬ 60 አቁስዬ (ጦርነት ለሚያውቅ ይህ የሚችና የቆሳይ አሃዝ ራሱ ውሸት መሆኑን ያረጋግጣል) ወደፊት እየተጓዝኩ ነው ብሎ ዋሽቷል ። ሞኝ ካለ ደግም ለጦሩ አዋጣ ሲባል እንዲገፈግፍ ለማድረግ ነው ። በመጀምሪያ ደረጃ ተጠቃ የተባለው ቃፍቲያ የወልቃይት መሬት እንጂ ትግራይ ተብሎ ለጸድቅላቸውየሚገባ አይደለም ። ግን ከከሃዲው ብርሃኑ ምን ይጠበቃል ? በሁለተኛ ደረጃ ወያኔ አርሶ አደሩን ትጥቅ አስፈታለሁ ብሎ በአካባቢው ከተሰማ መጠነና ተኩስ ውጪ ምንም ውጊያ አልነበረም ። ሶስተኛ ሻዕቢያ አሁን ባለበት የድቀቀ አቅም ወያኔን ሊተናኮል ከቶም የሚደፍር አይደለም ። አምባገነን ቢሆንም ፤ ጣጤም ቢባልም ኢሳያስ ራሱን ለውድቀት ጋባዥ ዕብድ አይደለም ። ከቃፍቲያ ወደ ሳጃም ጉዞ ሄሊኮፕተርን ጠያቂ ነው!! በመሰረቱ ግን የአርበኞች ግንባር ሰራዊት የሚባለው በቁጥር 40 በላይ አልነበረም/አይደለም ። ለዚህ የአፍ ጄኔራሉ አንዳርጋቸው የጨመረው ቁጥር ሀያ ሳይሞላ ዓመታት አልፈዋል ። ወያኔ ደግሞ--ያውም በተጠናከረበት በኤርትራ ድንበር አካባቢ--መኦት በማይሞላ ወታደር ሊጠቃ የሚችል እንዳልሆነ መገመት ከባድ አይደለም ። ውሎ አድሮ ከዚህ በፊት የብርሃኑ ድንፋታዎችና መግለጫዎች ሁሉ ውሸት ሆነው እንደተገኙት ይህም ቃፍቲያ ያዝን ወዘተ ቅጥፈት መሆኑ መጋለጡ አይቀርም ፡፤ ብርሃኑ እንደ ጎሹ ወደ ሀይማኖት ያመራ ይሆን? ለማየት ያብቃን !

የስፖርት ፌዴሪሽኑን ከአላሙዲና ወያኔ ጥቃት የተከላከልነውና ለነጌታቸው ደጀን የሆነው ፌዴሬሽኑ ለብርሃኑ እንዲሰጥ አልነበረም ። እነ ጌታቸው እንደ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የሆን ድርጅት ደጋፊና አብል ሙብታቸው የተጠበቀ ቢሆንም የስፖርት ፌዴሬሽኑን ግን ለአንድ ድርጅት ተገዢና መጠቀሚያ ለማድረግ ግን ሕዝብ አልፈቀደላቸውም ። ይህንን ጠንቅቀው ማወቅ ሲገባቸው አሻፈረን ብለው አሉ ። በዚህም የተነሳ ቢያስን ፕሬዚዳንቱን ምክትሉ ከቦታቸው ማንሳት የሁላችን ግዴታ ነው ። ይህንንም አውቆ ገቢራዊ ማድረግ ለፌዴሬሽኑ ህልውና ወሳኛ አስፈላጊም ነው ። ግንቦት 7 በፖለቲካው መድረክ ዋንቅ ተልዕኮው ሀገር አድን ትግሉን ማደናቀፍና ለወያኔ፤ ሻዕቢያና አሜሪካንም በቀጥታም በእጅ አዙርም መጥቀም ነውና ይህንን ጋሬጣ ህልውና መንሳቱም ግዳጃችን ሊሆን ይገባል ።

የስፖርት ፌዴሬሽናችን ከግንቦት 7 ቁጥጥር ይጽዳ !!